# FSS Update

የማኅበራዊ ጥናት መድረክ

Forum for social studies

Issue No. 28

July 2008

An email newsletter
to facilitate networking and information exchange among CSOs and researchers

## In This Issue:

- ደጃዝማች ወልደሰማዕት ገብረወልድና የወላይታ ልማት በቅድመ አብዮት ኢትዮጵያ
- DIASPEACE Kick-off Workshop Launched, p.3

## Just off the Press

### Academic Freedom in Ethiopia

Perspectives
of Teaching Personnel

Edited by Taye Assefa

## ደጃዝማች ወልደሰማዕት ገብረወልድና የወላይታ ልማት በቅድመ አብዮት ኢትዮጵያ

የማኅበራዊ ጥናት መድረክ (ማጥመ) ላለፉት ሁለት ዓመታት “ከድህነት ወደ ልማት፣ እውቀትን ለትውልድ ማስተላለፍ” በሚል መርህ ስር ሲያካሂድ የነበረው የሁለተኛ ዙር የውይይት መድረክ ማገባደጃ ላይ ደጃዝማች ወልደሰማዕት ገብረወልድ "Reforming Provincial *(Awraja)* Administration (1963-1972 GC): Reminiscences" በሚል ርዕስ ያዘጋጁትን ጽሁፍ ፍሬ ሀሳቦች በእንግድነት በተጋበዙበት ውይይት ላይ ሐምሌ 11 ቀን 2000 ዓ.ም. በግዮን ሆቴል በተደረገው ስብሰባ ላይ አቅርበዋል።



ደጃዝማች ወልደሰማዕት በሐረር ክፍለ ሀገር በአሰበ ተፈሪ ከተማ ተወልደው የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን እዚያው ከጀመሩ በኋላ ወደ አዲስ አበባ በመምጣት ተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት ያጠናቀቁ ሲሆን ቀጥሎም በኮተቤ ቀዳማዊ ኃ/ሥላሴ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ተምረው የእንግሊዝ የ2ኛ ደረጃ ትምህርት መልቀቂያ ፈተና ሲያልፉ በ1943 ዓ/ም ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ ገቡ። የኮሌጅ ትምህርታቸውን ሳያጠናቅቁ ለጥቂት ጊዜ በአየር ኃይል ካገለገሉ በኋላ በአገር ግዛት ሚኒስቴር ተቀጥረው የሚኒስትሩ የራስ አበበ አረጋይ ረዳት በመሆን ሰሩ። በዚሁ ስራ ላይ እያሉም በመላላክ ትምህርት ከእንግሊዙ የቤኔት ኮሌጅ የኢኮኖሚክስ ዲፕሎማ አገኙ። በ1948 ዓ/ም ወደ ቤይሩት ሄደው



እዚያ ከሚገኘው የአሜሪካ ዩኒቨርስቲ በህዝብ አስተዳደር የመጀመሪያ ዲግሪ አገኙ። ከዚያ ሲመለሱም መጀመሪያ የሐረር ክ/ሀገር የሕዝብ ፀጥታ ጥበቃ መምሪያ ዋና ዲሬክተር፣ ከዚያም የሕዝባዊ ኑሮ ዕድገት ሚኒስቴር የአስተዳደር ዋና ዲሬክተርና ቀጥሎም ረዳት ሚኒስትር በመሆን ሲያገለግሉ ቆይተው በ1955 ዓ/ም የወላይታ አውራጃ አስተዳዳሪ ሆነው ተሾሙ። እስከ 1964 ዓ/ም በአውራጃው ውስጥ ልዩ ልዩ የልማትና የአስተዳደር ለውጥ ያስመዘገቡበትን ስራ ሲሰሩ ቆይተው የወለጋ ክ/ሀገር አስተዳዳሪ (ያኔ እንደራሴ) ሆነው ወደ ምዕራብ ኢትዮጳያ ፊታቸውን አቀኑ። ነግር ግን አካባቢውን አጥንተው የወጠኑትን በስራ ለመተግበር ብዙም ዕድል ሳያገኙ የ1966 አብዮት ስለፈነዳ የአስተዳደር ሥራቸውን ለቀቁ።

ደጃዝማች ወልደሰማዕት በአፄ ኃ/ሥላሴ ዘመነ መንግስት በተለያዩ የአስተዳደር የኃላፊነት ቦታዎች ከመስራታቸው በተጨማሪ የኢትዮጵያ የቅርስ ባለአደራ



**Address:** FSS, P.O. Box 25864 code 1000, A.A., Tel. (251-11) 629 7888/91, Fax: (251-11) 629 7889
Email: fss@ethionet.et Web: www.fssethiopia.org.et

ማኅበር የቦርድ አባል ሆነው አገራቸውን አገልግለዋል፡፡ በተለይም በወላይታ አውራጃ አስተዳዳሪ ሆነው ለዘጠኝ ዓመታት ያህል በሰሩበት ዘመን ከጊዜው የቀደመ የልማት አሰራርንና የመንግስት አስተዳደርን የተገበሩ እጅግ ተወዳጅ የነበሩ የልማት ጀግና መሆናቸውን ውይይቱን የመሩትና በወላይታ አካባቢ የተለያዩ ምርምሮችን ያካሄዱት አቶ ደሳለኝ ራህማቶ አሳውቀዋል፡፡

ደጃዝማች ወልደሰማዕት በመጀመሪያ የቤተመንግስት አገልግሎት ዘመናቸው የአልጋ ወራሽ የቅርብ ረዳትና አማካሪ ሆነው በሚሰሩበት ወቀት ስለሀገራቸው ውስብስብ የማህበራዊ፣ የፖለቲካና የልማት ችግሮች በጥልቀት ለመመርመርና ለማወቅ መቻላቸው በቀጣይ የኃላፊነት ዘመናቸው ለሰፊ ስራ መነሻቸው እንደነበር ለውይይቱ ተሳታፊዎች በዝርዝር አቅርበዋል፡፡

በወላይታ አውራጃ ስላበረከቱት የልማትና የመልካም አስተዳደር ስራ ደጃዝማች ወልደሰማዕት ሲያብራሩ በአዲስ አበባ የሚገኙትን እንደ ግብርና፣ ቴሌኮሙኒኬሽን፣ አውራ ጐዳና፣ የመብራት ኃይልና የውሃ ልማት መሰል የመንግስት መስሪያ ቤቶችን በማወያየትና በማቀናጀት ውስን የነበረውን የመንግስት ሀብት፣ እውቀትና የሰው ኃይል ከአካባቢው ህዝብ ተሳትፎ ጋር በማስተባበር ለልማት መሰረት የሆኑትን አውታሮች በመዘርጋት ሰፊውን የልማት እንቅስቃሴያቸውን መጀመር እንደነበረባቸው በዝርዝር አስረድተዋል፡፡ ኢትዮጵያ አገራችን ፍትህና መልካም አስተዳደር እንጅ የውጭ እርዳታ አያስፈልጋትም በማለትም ለዘመናት በፍትህ እጦት፣ በሙስና እና እጅግ በተንዛዛ የመንግስት ቢሮክራሲ ይጉላላ የነበረውን የወላይታ ህዝብ በማወያየት፣ በመቀስቀስና ራሳቸውም አርአያ በመሆን መልካም አስተዳደርንና ፍትህን ለማስፈን በሚቻላቸው መጠን ከፍተኛ ጥረት ማድረጋቸውን አብራርተዋል፡፡

ደጃዝማች ወልደሰማዕት ገብረወልድ በወላይታ ከሰሯቸው የልማት ሥራዎች ውስጥ በጥናትና በማስተር ፕላን የተደገፉ 6 ከተሞችን መቆርቆር፣ በኢትዮጵያ 2ኛው የሆነውን የሬዲዮ መገናኛ በወላይታ ሶዶ ከተማ ማስተከል፣ ለከተማዋ ማስተር ፕላን እንዲዘጋጅና ዘመናዊ የውስጥ መንገዶችና ከወላይታ ወረዳዎች ጋር በአውራ ጎዳናዎች ማገናኘት፣ የመብራት፣ንፁህ የመጠጥ ውሀ (በቧንቧ)፣ የሆስፒታልና የት/ቤቶች፣ የመሰብሰቢያ አዳራሽና የቤተ መጻሕፍት፣ የፖሊስና የፍርድ ቤቶች ተጠቃሚ ማድረግ፣ የወላይታ አውራጃን አጠቃላይ ካርታ ማዘጋጀትና ለልማት በሚያመች መልክ በወረዳዎች መከፋፈልና የልማት አውታሮችን መዘርጋት፣ ለኦሞ ወንዝ ድልድይ መዘርጋት፣ ንፁህ የመጠጥ ውሀ በቧንቧ እንዲዳረስ ማድረግ፣ የሕዝብ መዋጮ ለግለሰቦች መጠቀሚያነቱን በማስቀረት ህዝቡ ራሱ እየተቆጣጠረው መልሶ የተለያዩ ት/ቤቶች፣ ሆስፒታልና ክሊኒኮች ለመሳሰሉት የሕዝብ ልማትና አገልገሎት ማቋቋምያ ሥራ እንዲውል ማድረግ፣ በጥናትና በባለሙያ የተደገፈ የእርሻ፣ የእደጥበብ፣ የኢንቨስትመንትና የሠፈራ መርሀ ግብር መተግበር የመሳሰሉትን በጥቂቱ ለአብነት መጥቀስ ይቻላል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ፍትሕን በማስፈን ረገድ ዜጎች ያላግባብ እንዳይታሰሩ ወይም ህግ ከሚፈቅደው በላይ በእስር ቤት እንዳይቆዩ፣ ዳኝነት እንዳይዛባና ሰዎች በሀሰት ምስክርነት ወይም በሙስና ፍትሕ እንዳይጓደልባቸው፣ በቀጠሮ መራዘምና መበራከት ባለጉዳዮች በመንግስት መ/ቤትም ሆነ በፍርድ ቤት እንዳይጉላሉ፣ ፖሊሶችም ሆኑ ዳኞች በስልጣናቸው ስር ላሉ ሰዎች መጉላላት ተጠያቂ የሚሆኑበትንና ተበዳዮች የሚካሱበትን የአሰራር ስርዓት በማበጀት አስተዳደሩን ፍትሃዊ ለማድረግ ጥረዋል፡፡ በጭሰኝነት ቀንበር ስር ያሉ ዜጎችን ለመታደግ አመቺ የሰፈራ ቦታዎችን በመምረጥና እስከ 5 ሄክታር መሬት በየአባወራው ለአራሾች በማከፋፈል ራሳቸውን መቻል ብቻ ሳይሆን ትርፍ አምራችና ለገበያ አቅራቢም እንዲሆኑ አስችለዋቸዋል፡፡ በተለይ የሰፈራዎቹ ውጤታማነትና የአውራጃው ሌሎች የልማት ክንዋኔዎች ዝና ከኢትዮጵያ ውጭ ስለናኘ የዓለም ባንክ ፕሬዚዳንት የነበሩት ሮበርት ማክናማራ፣ የስዊድን የልማት ተራድዖ (ሲዳ) ሃላፊ የነበሩትና የስዊድን የፓርላማ አባላት ልዑካን ይህንኑ የሰሙትን በዐይናቸው ለማየት ወላይታ ድረስ ለጉብኝት መሄዳቸው ለውጤቱ አስደናቂነት ምስክሮች ነበሩ፡፡ በተለይ የማክናማራ ጉብኝት በኋላ ላይ ለወላይታ የእርሻ ልማት ድርጅት (ዋዱ) በባንኩ ድጋፍ መቋቋም መሰረት የጣለ ነበር፡፡ ለግል ባለሀብቶችም በስራ ላይ ያልዋለ የመንግስት መሬት በማቅረብ በእርሻ መሳሪያዎችና የግብርና ግብዓቶች የሚደገፉ ዘመናዊና ሰፋፊ እርሻዎች በስዊስና በፈረንሳይ ኩባንያዎች እንዲጀመሩና በኢትዮጵያ ውስጥ ከባራቶላ ቀጥሎ 2ኛው አትክልት ለውጭ ገበያ የሚያቀርብ እርሻ እንዲቋቋም፣ የትምባሆ ሞኖፖልም የራሱን እርሻ እንዲያቋቁም አመቻችተዋል፡፡

በውይይቱ ጊዜ የተለያዩ ተሳታፊዎችም ስለደጃዝማች ወልደሰማዕት የልማት ስራዎች የሚያውቁትን የራሳቸውን ምስክርነትና ለሳቸው ያላቸውን ጥልቅ ፍቅርና ከበሬታ የገለፁ ሲሆን ሌሎች ደግሞ በወቅቱ ስለጋጠሚቸው መሰናክሎች





ጥያቄ አቅርበው ምላሽ ተሰጥቶአቸዋል፡፡ አንዳንድ ተዋያዮችም የደጃዝማችን አርአያነት ያለው የልማትና የአስተዳደር ሥራ በህትመትና በሚዲያ በስፋት እንዲሰራጭ ማጥመን ተማፅነዋል፡፡ ደጃዝማች ወልደሰማዕትም በአስተዳደርና በልማት ስራ ስለነበራቸው ተሞክሮ ለትውልድ ለማስተላለፍ ዳጎስ ያለ መፅሀፍ በማዘጋጀት ላይ መሆናቸውን በዚሁ አጋጣሚ ለተሰብሳቢው ገልፀዋል፡፡

የማጥመ ስራ አስፈፃሚ ዲሬክተር ፕ/ሮ ባህሩ ዘውዴ በውይይቱ መዝጊያ ንግግር ላይ ለሁለት ተከታታይ ዓመታት ሲካሄድ የነበረው «ከድህነት ወደ ልማት፣ ዕውቀትን ለትውልድ ማስተላለፍ» በሚል ስያሜ የሚታወቀው መርሀ ግብር አላማው በሃያኛው ክፍለ ዘመን በልማት መስክ፣ በፖሊሲ ቀረጻና በአመራር ደረጃ በመንግስት መስሪያ ቤቶች እንደዚሁም በግሉ ዘርፍ ሲሰሩ ከነበሩ



በርካታ አንጋፋ ኢትዮጵያውያን መሀከል አንዳንዶቹን በመጋበዝ እውቀታቸውንና ልምዳቸውን ለተተኪው ትውልድ

እንዲያካፍሉ ማድረግ እንደነበር ገልጸው እስከዛሬ በየሁለት ወሩ በሚካሄደው በዚህ ውይይት ቁጥራቸው ወደ ሃያ የሚጠጉ በተለያዩ የሙያ ዘርፍ የተሰማሩ አንጋፋ ኢትዮጵያውያንን የዳበረ ልምድና እውቀት ለህብረተሰቡ እንዲያካፍሉ የማህበራዊ ጥናት መድረክ ማስቻሉንና ጽሁፎቻቸውም መታተማቸውን ገልጸዋል። በመጨረሻም ፕ/ሮ ባህሩ ዘውዴ በውይይቱ መድረክ ላይ ጽሁፍ ላቀረቡት አንጋፋ ባለሙያዎች፣ ለፕሮግራሙ አስተባባሪ ለአቶ ሺፈራው በቀለ፣ እንዲሁም ለማጥመ ሠራተኞች፣ ለውይይቱ ተሳታፊዎችና ለጋሽ ድርጅቶች ምስጋናቸውን አቅርበዋል።

## DIASPEACE Kick-off Workshop Launched

DIASPEACE is the short label for a research project titled "Diasporas for Peace: Patterns, Trends and Potential of Long-distance Diaspora Involvement in Conflict Settings: Case Studies from the Horn of Africa." The project intends to generate evidence-based and policy-relevant knowledge on the impact of Diaspora activities on conflict and peace-building by studying Diaspora networks in Europe and their transnational activities in the Horn of Africa, namely, Ethiopia, Eritrea, and Somalia. The project, which is expected to last for three years, is funded by the Social Science Research Program of the European Union.

The DIASPEACE kick-off workshop was held in Brussels from 5 - 6 May 2008. Representatives of eight partner institutions that constitute the research consortium attended the kick-off meeting, which was designed to bring the researchers together and deliberate on research objectives, key research questions/concepts, research methods, literature review, work plan, and project management. The members of the consortium come from six European countries and two countries in the Horn of Africa. The eight partner institutions include University of Jyväskylä (Finland), Bonn International Center for Conversion (Germany), Max Planck Institute for Social Anthropology (Germany), International Peace Research Institute (Norway), African Diaspora Policy Center (The Netherlands), Centro Studi di Politica Intenazionale (Italy), the Forum for Social Studies (Ethiopia), and Academy for Peace and Development (Somaliland).

During the kick-off meeting, FSS was represented by Dr. Kassahun Berhanu and Dr. Gebre Yntiso, who will undertake the fieldwork in Ethiopia with Professor Bahru Zewde as team leader. The research project, which involves different phases and milestones, is expected to produce a series of deliverables (reports and publications) to be co-authored by the partner institutions and researchers.

## New Publication from FSS

